# ለመሪው የተዘጋጀ

## (ቅባት በመጽሐፍ ቅዱስ) ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጣ

1. ስለ ቅባቱ አዘገጃጀት፣ ምንና ማን እንደሚቀባ፣ በቅባቱ የተቀባ እጅግ እንደሚቀድስ፣ በዚህ ዓይነት አዘገጃጀት ሌላ መዘጋጀት እንደሌለበት፣ ያንን በመሰለ ንጥረ ነገሮች ሌላ ያዘጋጀም ሆነ ከካህናት ሌላ የቀባ እንዲገደል፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር ቅባቱ እቃዎችንና ካህናትን ለእግዚአብሄር ለመቀደስ ይውላል፡፡
2. ዕቃዎቹ የሚቀቡበት ምክንያት እጅግ የተቀደሱ (ለእግዚአብሄር የተለዩ) እንዲሆኑ ሲሆን አሮንና ልጆቹ ደግሞ እግዚአብሄርን ለማገልገል እንዲቀደሱ (እንዲለዩ) ነው፡፡ ክህነታቸው እስከሚመጡት ትውልዶች ሁሉ የሚቀጥል እንደሆነ ይነግረናል፡፡
3. እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ነገሥታትና ነብያት ናቸው፡፡
4. አማኞች ካህናት መሆናቸውን እነዚህ ክፍሎች ሁሉ የሚያረጋግጡት ሃሳብ ነው፡፡
5. የብሉይ ኪዳን ካህናት ውጫዊ ቅባት እንደሚቀቡ፤ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን በውስጣችን እንዲሆኑ በመስጠት ማረጋገጫና ለአገልግሎታችን ብቃት የሚሆን ቅባት አድርጎ ሰጥቶናል፡፡ ሉቃ4፡18፣ ሥራ10፡38፣ 2ኛ ቆሮ1፡21 ተመልከት፡፡
6. የተቀባ የሚለው ‹‹እኛንም እናንተንም›› በማለት ስለአማኞች ነው የሚናገረው፡፡ ቀቢ በመሆን ደግሞ በዚህ ክፍል የተነገረለት ራሱ እግዚአብሄር ነው፡፡ ይህ በ1ኛ ዮሐ 2፡20 ና 27 ላይ ያለው ክፍል እኛ ሁላችን ቅባቱ በውስጣችን ሁልጊዜ እንደሚኖርና ቅባቱንም ደግሞ የተቀበልነው ከእርሱ ማለትም ከእግዚአብሄር እንደሆነ በማያወላውል መንገድ ያረጋግጣል፡፡
7. በብሉይ ኪዳን የተወሰኑ ሰዎች ይቀባሉ በአዲስ ግን አማኞች በሙሉ ቅባቱ አላቸው፣ በብሉይ እግዚአብሄር ይመርጥና ሊቀካህኑ ይቀባል፣ በአዲስም በእግዚአብሄር የተመረጡትን በሊቀካህኑ በክርስቶስ በኩል ይቀባሉ፣ በብሉይ ቅባቱ ውጫዊ ሲሆን በአዲስ ግን ውስጣዊ ነው፤ በብሉይ ቅባቱ ሰው የሚያዘጋጀው ሲሆን በአዲስ ግን ቅባቱ ራሱ እግዚአብሄር ነው፤ ቅባቱ በብሉይም በአዲስም ለእግዚአብሄር የሚቀድስ ነው…ወዘተ፡፡
8. በተለየ መንገድ ለሌሎች በበለጠ ሁኔታ የተቀባ አለ ማለት ካስፈለገ ይህ ሰው ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡
9. ስለቅባት ብዙ የሚሰሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የማይገኝላቸው ሃሳቦች ይሰማሉ፤ ለምሳሌም በየጊዜው ቅባት ለመቀበል ጸሎት፣ አንዳችን ከሌላችን የበለጠ ቅባት እንዳለንና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ እግዚአብሄር ሁላችንንም በመንፈሱ ቅባት የቀባን እንደሆነና ይህም ቅባት ለጌታ ተቀድሰን የእርሱን በጎነት የምንናገርበተንና የማስታረቅ አገልግሎት እንድናከናውን ሃይል ይሆነናል፡፡